የኢትዮጵያ
ብሔራዊ ባንክ
NATIONAL BANK
OF ETHIOPIA

# በማዕከል እና ክልሎች በሚገኙ የወርቅ ግዥ ማዕከላት በኩል የሚገዛውን ወርቅ በተመለከተ የተደረገ የዋጋ ማሻሻያ መመሪያ ቁጥር ከማዳ 1/2016

## መግቢያ

በባህላዊ የወርቅ ምርት ዘርፍ በሚስተዋሉ በርካታ ችግሮች ምክንያት አገሪቱ ማግኘት የነበረባት የውጭ ምንዛሪ እና ሌሎች ከዘርፉ የሚጠበቁ በርካታ ገቢዎች ከሚጠበቀው በታች እየወረዱ በመምጣታቸው እንደ አገር የሚጠበቀውን ውጤት ማግኘት ያለመቻሉ፣

ለወርቅ አቅራቢዎች የሚከፈለው ማበረታቻ ተወዳዳሪ ባለመሆኑ ለባንኩ መቅረብ የነበረበት ወርቅ በሕገ-ወጥ መንገድ በኮንትሮባንድ ገበያ እንዲሸጥ ምክንያት መሆኑ በመረጋገጡ፣

በመሆኑም፣ ለወርቅ አቅራቢዎች የተሻለ የዋጋ ማበረታቻ በመስጠት እና አቅርቦትን በማሻሻል ከውጭ ምንዛሪ ግኝት አኳያ ከባህላዊ የወርቅ ዘርፍ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ ማሳደግ እንዲቻል በስራ ላይ ያለውን የወርቅ ዋጋ ማበረታቻ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህ የውስጥ አሰራር መመሪያ ተሻሽሎ ወጥቷል።

## አንቀጽ 1፡ አጭር ርዕስ

ይህ ማሻሻያ ደንብ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የወርቅ የግብይት ዋጋን አስመልክቶ የተሻሻለ የአሰራር መመሪያ ቁጥር 1/2016 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## አንቀጽ 2፡ ማሻሻያ

የወርቅ መግዥያ ዋጋ የተደነገገበት መመሪያ ቁጥር 3/2015 በአንቀጽ 2 ከንዑስ አንቀጽ 2.1 እስከ 2.4 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች ተሰርዘው፣

ሀ) በአንድ ጊዜ ከ50 ግራም ጀምሮ እስከ 3 ኪ.ግራም ወርቅ ለባንኩ ለሚያቀርቡ አቅራቢዎች በዓለም ገበያ ዋጋ ላይ 60% ማበረታቻ ጭማሪ እየተደረገ ግዢው ይፈጸማል፣



ብሔራዊ ባንክ NATIONAL BANK OF ETHIOPIA

ለ) በአንድ ጊዜ ከ3.01 ኪ.ግራም ጀምሮ እስከ 30 ኪ.ግራም ወርቅ ለባንኩ ለሚያቀርቡ አቅራቢዎች በዓለም ገበያ ዋጋ ላይ 67% ማበረታቻ ጭማሪ እየተደረገ ግዢው ይፈጸማል፣

ሐ) በአንድ ጊዜ ከ30.01 ኪ.ግራም በላይ ከአቅራቢዎች በመሰብሰብ (Aggregator) ወርቅ ለባንኩ ለሚያቀርቡ አቅራቢዎች በዓለም ገበያ ዋጋ ላይ 72% ማበረታቻ ጭማሪ እየተደረገ ግዢው ይፈጸማል፣

መ) እላይ ከተሻሻሉት አንቀጾች በስተቀር ከዚህ በፊት በነባሩ መመሪያዎች ተጠቅሰው የሚገኙ አንቀጾች ተግባራዊ እየተደረጉ ይቀጥላሉ፡፡

## አንቀጽ 3፡ ተፈጻሚነት

ይህ ማሻሻያ ከሰኔ 10 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ**

ማሞ እስመለዓለም ምህረቱ
ገዥ